# አፍሪካ፡- በግጭት የታጀቡ ምርጫዎች አሳሳቢውን የመብቶች ሁኔታ አመላካች ናቸው

*የመንግስታት ያልተገባ ጣልቃ ገብነትና፣ የተዳከሙ ተቋማት የዲሞክራሲ ሂደቱን ያጓትታሉ*

(ጆሀንስበርግ፣ ጥር 13 ቀን 2004) - ባለፈው የአውሮፓውያን ዓመት 2011 ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት በሙሉ የተካናወኑ ምርጫዎች የሀገራቱን እያደገ የመጣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የማስፈን ፍላጎተ ያመላከቱ ቢሆንም የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ግን በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ ሃይልን በመጠቀም በምርጫ ወቅቶችና ከዚያም በኋላ መብቶችን ገድበዋል ሲል ሂዩማን ራይትስ ዎች ዛሬ ባወጣው *የ2012 የዓለም ሪፖርት* ገለጸ።

በ 2011 በኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ በላይቤሪያ፣ በናይጀሪያ፣ በዩጋንዳ፣ በዛምቢያ እና በሌሎችም ከሰሀራ በታች በሚገኙ ሀገራት ፕሬዚዳንታዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል። በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ እና በዩጋንዳ የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች በተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎች ላይ ከልክ ያለፈ ሃይል ተጠቅመዋል፤ እንደዚሁም ጋዜጠኞችን፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ዕጩዎችን፣ የሲቪል ማህበራት መሪዎችን እና ሰላማዊ ዜጎችን የጥቃት ዒላማቸው አድርገዋል። በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ከምርጫ በፊትና ከድምጽ መስጫ ቀን በኋላ በነበሩት ጥቂት ቀናት በአንዳንድ አካባቢዎች ወታደሮች የተቃዋሚ ደጋፊዎች ናቸው በተባሉ ሰዎች ላይ በከፈቱት ተኩስ ቢያንስ 42 ሰዎች ተገድለዋል። በአንዳንዶቹ ሀገራት በ2010 በተካሄዱ ምርጫዎች ወቅት የተነሱ ግጭቶች ውጤቶች በ 2011ም ተንጸባርቀዋል።

"ይህ ያሳለፍነው ዓመት በርካታ አፍሪካውያን መሪዎቻቸውን በሰላማዊና በትክክለኛ መንገድ ለመምረጥ ያላቸውን ፍላጎት ያሳየ ነው።" ያሉት ዳንኤል በቀለ የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ዳይሬክተር "ይሁንና ምርጫዎቹ በመንስግት ወከባዎች፣ የጦር ሰራዊትና የፖሊስ ሃይሎች በፈጸሚቸው ማንገላታቶችና በግጭቶች የታጀቡ መሆናቸው አሳዛኝ ነው። እነዚህ አሳሳቢ ችግሮች መፍትሄ የማይሰጣቸው ከሆነ አፍሪካውያን በቀጣይ ምርጫዎችም መሰል ችግሮችን ማየታቸው የማይቀር ነው።"

676 ገጾች ባሉት በዚህ ሪፖርቱ ሂዩማን ራይትስ ዎች ብዙዎች ይሆናል ብለው ያልገመቷቸው ሕዝባዊ መነሳሳቶች የታዩባቸውን በአረቡ ዓለም የሚገኙ ሀገራትን ጨምሮ ከዘጠና በላይ በሚሆኑ ሀገራት ባለፈው ዓመት በሰብአዊ መብቶች ረገድ የተደረጉ መሻሻሎችን ገምግሟል። ሂዩማን ራይትስ ዎች በሪፖርቱ እንዳለው የ "አረቡን መነሳሳት" በሃይል ለመቋቋም የተሰለፉ ሀይሎች ያሉ በመሆኑ በዚህ አካባቢ መብቶችን የሚያከብሩ ዲሞክራሲያዊ መንግስታት እንዲፈጠሩ ለማገዝ ዓለማቀፉ ማህበረሰብ ጠቃሚ ሚና ይጫወታል።

በአፍሪካ በኮትዲቯር በህዳር ወር 2010 የማጣሪያ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ከተደረገ በኋላ በምርጫው የተሸነፉት የሀገሪቱ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ሎረን ባግቦ ስልጣናቸውን ለአሸናፊው አላሳን ኡዋታራ ለማስረከብ ፈቃደኛ አልነበሩም። ይህ ደግሞ ለስድስት ወራት ለዘለቀውና ቢያንስ 3000 ሰዎች ለተገደሉበት ግጭት መቀስቀስ ምክንያት ሆኗል። በአሁኑ ጊዜ ባግቦ ዘ ሄግ በሚገኘው ዓለማቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ፍርዳቸውን በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። ይህም የዓለማቀፍ ፍትሕ አፈጻጸም እየሰፋ መሄድ ማሳያ ነው። ይሁንና አሁን የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ለሆኑት ኡዋታራ ታማኝ በሆኑ ሃይሎች የተፈጸሙ ከባድ ወንጀሎችን ለመቅጣት በኮትዲቯርም ሆነ በዓለማቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት የተደረገ ጥረት የለም።

በሚያዝያ ወር 2011 የተካሄደውን የናይጀርያ ምርጫ ብዙዎች በሀገሪቱ ታሪክ ከተደረጉ ምርጫዎች ሁሉ ትክክለኛው ነው በማለት ገልጸውት ነበር። ይሁን እንጂ ቢያንስ 165 ሰዎች በምርጫ ዘመቻ ወቅት በተቀሰቀሱ ግጭቶች ሲገደሉ በፕሬዚዳንታዊ ምርጫው ወቅት በሰሜናዊ ናይጀርያ የተነሳው ረብሻና አንጃ ተኮር ግድያ ደግሞ ከስምንት መቶ በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን እንዲያጡ ምክንያት ሆኗል። በእነዚህ ወንጀሎች ተጠያቂ የሆኑ ሰዎችን ናይጀርያ ለፍርድ አላቀረበችም።

ጊኒ እና ብሩንዲም በ 2010 ምርጫ አካሂደዋል። ይሁንና በእነዚህ ሀገራት በ 2011 የታዩት ሁኔታዎች የፍትሕ ሥርዓቶቻቸውን የማጠናከርን፣ በጸጥታ ሃይሎቻቸው አባላት የሚፈጸሙ ስር የሰደዱ ከሕግ ያፈነገጡ ድርጊቶችን የማስቆምንና ወደ አንድ ፓርቲ አገዛዝ ቀስ በቀስ የመሄድን አዝማሚያ የመግታትን አስፈላጊነት ያሳዩ ነበሩ። በሩዋንዳም ተቃውሞ ፖለቲካን ለማስተናገድ ያለው የፍላጎት ማጣት በ 2010 ከተካሄደው ምርጫ በኋላም አልተቀየረም። ኬንያም በአደባባይ ከዓለማቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ጋር ብትተባበርም በ2007 በሀገሪቱ ከተካሄደው ምርጫ ጋር ተያይዞ ተከስቶ የነበረውን ግጭት በማነሳሳት ተሳትፈዋል ተብለው የተጠረጠሩ ስድስት የፖለቲካ መሪዎችና ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች ለፍርድ እንዳይቀርቡ ለማድረግ ልዩ ልዩ የሕግና የፖለቲካ መንገዶችን ተጠቅማለች።

በጥር 2011 ለደቡብ ሱዳን ነፃነት በሱዳን ሕዝበ ውሳኔ ተካሂዷል፤ በሕዝበ ውሳኔውም ደቡብ ሱዳናውያን ለሁለት አስርት ዓመታት ከተካሄደው ጦርነት በኋላ በ 2005 በተፈረመው የሰላም ስምምነት መሠረት ከሰሜን ሱዳን ለመገንጠል በከፍተኛ ድምጽ ወስነዋል። ደቡብ ሱዳንም 54ኛ የአፍሪካ ሀገር ያደረጋትን ነፃነቷን በሐምሌ 2011 በይፋ አግኝታለች። ይሁንና ሀገሪቱ ከባድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች ይጠብቋታል። ምንም እንኳ የደቡብ ሱዳን መገንጠል አንጻራዊ በሆነ ሰላማዊ ሁኔታ ቢከናወንም የሱዳን መንግስት ሃይሎች ተደጋጋሚ ግጭት በሚከሰትባቸው ከደቡብ ሱዳን በስተሰሜን በሚገኙት ብሉ ናይል እና ደቡባዊ ኮርዶፋን በተባሉ

ግዛቶች የሚገኙ ቦታዎችንና አቢዬ በሚባለው አወዛጋቢ የድንበር አካባቢ በሚኖሩ ሰላማዊ ሰዎች ላይ ጥቃት ስንዝረዋል። ከዚህ በተጨማሪም የሱዳን መንግስት በዳርፉር በሰላማዊ ሰዎች ላይ አዲስ ጥቃት አድርሷል። በዳርፉር ለተፈጸሙ ወንጀሎች የሱዳኑን ፕሬዚዳንት ኦማር ሐሰን አልበሽር ለፍርድ ለማቅረብ በዓለማቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት የተቆረጠው የመያዣ ትዕዛዝ አሁንም እንዳለ ነው።

ዓመቱን በሙሉ ሶማሊያ፣ሰሜናዊና ምስራቃዊ ኮንጎ እንዲሁም የሱዳን አንዳንድ አካባቢዎች በጦርነት እና በሰብአዊ ቀውሶች ተመተዋል። ይህም ኢኮኖሚያዊ ችግሩን ያባባሰው ሲሆን የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የአፍሪካ ህብረት ዓለማቀፍ የሰላም አስከባሪዎችን እንዲያሰማሩ አድርጎአቸዋል። በደቡብ ሱዳን ብቻ ከ 2600 በላይ ሰዎች በግጭቶቹ ተገድለዋል። በሶማሊያ ደግሞ መገናኛ ብዙሃን ወደ 2500 የሚጠጉ ሰዎች መገደላቸውን ዘግበዋል፤ ነገር ግን ቁጥሩ ከዚህ በላይ እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይደለም። ሂዩማን ራይትስ ዎች እነዚህ መንግስታት፣ ዓለማቀፍ ሃይሎች እና ታጣቂ የተቃዋሚ ቡድኖች በአባሎቻቸው የሚፈጸሙ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን እንዲያስቆሙ ጥሪ አቅርቧል። መንግስታትም ምርመራ ማካሄድና በጦር ወንጀሎች ተሳታፊ የሆኑ በሃላፊነት እንዲጠየቁ ማድረግ አለባቸው። ዓለማቀፍ ሃይላት በተለይ ሰላማዊ ሰዎችን ከጥቃት ለመጠበቅና ተፈናቃይ ወገኖችን ለመርዳት ካሁኑ የበለጠ አቅም መመደብ ይኖርባቸዋል ብሏል ሂዩማን ራይትስ ዎች።

በአሁኑ ወቅት በሰሜናዊ ምስራቅ ኮንጎ፣ በደቡብ ሱዳን እንዲሁም በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘውን ሎርድስ ሬዚስታንስ አርሚ የሚባለውን እጅግ አስከፊ ወንጀሎች የሚፈጽም የዩጋንዳ ተቃዋሚ ቡድን በመዋጋት ላይ የሚገኙትን የአካባቢው ሀገራት የጦር ሃይሎች ለማገዝ ዩናይትድ ስቴትስ 100 ወታደራዊ አማካሪዎችን ወደ አካባቢው ልካለች። በበርካታ የሶማሊያ አካባቢዎች አስከፊ የሆነ አገዛዝ ያሰፈነውን አል ሸባብ የተሰኘ እስላማዊ ታጣቂ ቡድን ለመደምሰስ ኬንያ እና ኢትዮጵያ ሠራዊቶቻቸውን ወደ ሶማሊያ አስገብተዋል።

ዳንኤል በቀለ እንደሚሉት “በአፍሪካ በሚደረጉት ጦርነቶች የሚሳተፉት ሁሉም ሃይሎች የሰላማዊ ሰዎች ሁኔታ ብዙም ግድ የሚሰጣቸው አይደሉም።” “በይነ መንግስታት አካላትና ተሰሚነት ያላቸው ሀገራት ሰላማዊ ሰዎችን በጦርነቶች ወቅት ከሚደርሱ ዘርፈ ብዙ ጉዳቶች ለመጠበቅ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ አለባቸው።”

ሂዩማን ራይትስ ዎች እንደሚለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶችን ማሟላት ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት ትልቅ ፈተና ሆኖ ይገኛል። የእናቶችና ሕፃናትን ጤንነት ለመጠበቅ መንግስታቱ ቁርጠኝነታቸውን ቢገልጹም የተሻሉ አገልግሎቶችን ለማቅረብ አቅሙ ባላቸው እንደ ደቡብ አፍሪካ እና ኬንያ ባሉ ሀገራት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ከወሊድ ጋር የተያያዙ ሞት እና የአካል ጉዳቶች መፍትሄ ሳይሰጣቸው ቀጥለዋል። ኬንያን ጨምሮ በመላ አህጉሪቱ የህፃናት ጤና አገልግሎት ተደራሽነት በቂ አይደለም።

ሌሎች በሀብት የታደሉ እንደ ኢኳቶርያል ጊኒ፣ አንጎላ፣ ናይጄርያ እና ጊኒ ያሉ ሀገራት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ማህበራዊ ደህንነትን ለማስፈንና ሙስናን ለመዋጋት የሚያውሉት እጅግ ጥቂቱን ነው። ይህንንም የሚያደርጉት በሕዝቦቻቸው ማህበራዊና አኮኖሚያዊ መብቶች ኪሳራ ነው። በአንዳንድ የዕድገት ማሳያዎች ሩዋንዳ እና ኢትዮጵያ መሻሻል ያሳዩ መስሎ ይታያል። ይሁንና በሁለቱም ሀገራት ያሉት አፋኝ መንግስታት የሀገር ውስጥ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾችን አጥቅተዋል እንዲሁም ጋዜጠኞችን፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን እና ሌሎች መንግስትን ይቃወማሉ ተብለው የሚታሰቡ ወገኖችን ለእስር ዳርገዋል።

ብዙ ሀገራት በተለይም ቻይና እና ሕንድ በአፍሪካ አህጉር ያላቸውን ተሳትፎ አጠናክረዋል። እያደገ የመጣው የእነዚህ ሀገራት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለአፍሪካ መንግስታትና ለሕዝቦቻቸው የኢኮኖሚ ዕድሎችን የፈጠረ ቢሆንም በተለይ ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ሕዝቦችን በሚመለከት ግን ስጋቶችን ማስነሳቱ አልቀረም። ለምሳሌ በደቡብ ሱዳን እና በኢትዮጵያ ነዋሪዎች ሲጠቀሙባቸው ከነበሩ መሬቶች በሃይል እንዲነሱ ተደርገው መሬቶቹ ለንግድ ግብርና ለኢንቨስተሮች ተሰጥተዋል። ይህም የነዋሪዎችን የምግብ ዋስትና ሊጎዳ የሚችል ነው።

በዛምቢያ በሚገኙ በቻይናውያን ባለቤትነት በተያዙ የመዳብ ማዕድን ማውጫዎች የሚሰሩ ሠራተኞች የሚደርስባቸው መልካም ያልሆነ አያያዝ እና በማሊ በወርቅ ማዕድን ማውጫዎች የሚሰሩ ህፃናት ሰራተኞች ለሜርኩሪ እንዲጋለጡ መደረጋቸው ሠራተኞች በሥራ ላይ ከሚደርሱባቸው የከፉ አደጋዎች ለመከላከል የተጠናከረ ጥበቃ የማድረግን አስፈላጊነት አጉልቶ ያሳየ ነው። የቤት ውስጥ ሠራተኞችን አያያዝ የሚገዛ ዓለማቀፍ ስምምነት እንዲፈጠር የአፍሪካ መንግስታት በተለይ የመሪነት ሚና ተጫውተዋል። በህፃናት የቤት ሠራተኞች ላይ የሚፈጸም ተገቢ ያልሆነ አያያዝ በአህጉሪቱ ተንሰራፍቶ የሚገኝ ችግር ነው።

“የአረብ መነሳሳት” ዜጎች የመሰብሰብ፣ የመደራጀትና ሐሳብን በነፃ የመግለጽ መብቶቻቸውን ለመጠቀም በሞከሩባቸው ከሰሃራ በታች በሚገኙ ሀገራትም በጸጥታ አስተጋብቷል። ሰፊ ዓለማቀፍ ሽፋን ባያገኙም አምባገነናዊ አገዛዝን፣ ፖለቲካዊ የፍትሕ እጦትን እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመቃወም በአንጎላ፣ በጊኒ፣ በኬንያ፣ በማላዊ፣ በሴኔጋል፣ በሱዳን፣ በስዋዚላንድ እና በዩጋንዳ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ተካሂደዋል። እነዚህ ተቃውሞዎች ከኬንያ በስተቀር በሁሉም ሀገራት በሃይል እንዲከሸፉ ተደርገዋል።

በ 2012 ምርጫ ሊካሄድ በታቀደበት በዚምባብዌ ባለስልጣናት በመካከለኛው ምስራቅ የተከሰቱትን ሁነቶች የሚያሳይ ፊልም ሲመለከቱ የነበሩ ተሚጋቾችን እስር ቤት አስገብተዋል፤ በርካታ ዚምባብዌያውያን የማዋከብ እና የሕገ ወጥ እስራት ሰለባዎች ሆነዋል። ለ 2012 ምርጫ በዝግጅት ላይ በምትገኘው ሴኔጋልም ፕሬዚዳንቱን በስልጣን ለማቆየት ታስቦ የተዘጋጀውን የሕገ መንግስት ማሻሻያ በመቃወም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። የሴኔጋል መንግስት የሲቪል ማህበረሰብ መሪዎችን አሳደደ። በአፍሪካ የተረጋጋ ዲሞክራሲ ተምሳሌት ተደርጋ ብዙ ጊዜ በምትጠቀሰው ሴኔጋል ይህ መከሰቱ አሳሳቢ ምልክት ነው። ሌላዋ የአህጉሪቱ የተስፋ ምልክት በሆነቸው ደቡብ አፍሪካ ሥራ ላይ ከዋለ ሀሳብን በነፃ የመግለጽና የሕዝብን መረጃ የማግኘት መብቶች ሊገድብ የሚችል የመረጃ ጥበቃ ሕግ በፓርላማው ጸድቋል።

" 'የአረብ መነሳሳት' የመካካለኛው ምስራቅ እና የሰሜን አፍሪካ ሕዝቦች ለነፃነትና ሰብአዊ ክብር ያላቸውን ፍላጎት ያሳየ ነው።" ያሉት ዳንኤል በቀለ "ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገራት ያሉ ሕዝቦችም መሰል ፍላጎቶች አሏቸው። በእነዚህና በሌሎችም አካባቢዎች ያሉ መንግስታት እነዚህን ፍላጎቶች ማክበር አለባቸው።" ብለዋል።

**የ 2012ን የዓለም ሪፖርት ለማንበብ፡ http://www.hrw.org/world-report-2012 ይጎብኙ።**

**አፍሪካን የሚመለከቱ ሌሎች የሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርቶች ለማግኘት፡ http://www.hrw.org/africa ይጎብኙ።**

**ለተጨማሪ መረጃ፡-**


ኒው ዮርክ፣ ዳንኤል በቀለ (አማርኛ፣ እንግሊዝኛ) ፡ +1-212-216-1223 ወይም +1-917-385-3878 (ሞባይል) ወይም በኢሜይል danielb@hrw.org

ኒው ዮርክ፣ ሮና ፔሊጋል (እንግሊዝኛ) ፡ +1-212-216-1232፤ +1-917-363-3893፤ ወይም በ ኢሜይል peligar@hrw.org

ጆሃንስበርግ፣ ሲኬ ካሳምባላ (እንግሊዝኛ) ፡ +27-79-22-05-254 (ሞባይል) ፤ ወይም በኢሜይል kasambt@hrw.org (ደቡብ አፍሪካን በሚመለከት)

ዋሽንግተን ዲ.ሲ.፣ ኮሪን ዳፍካ (እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ) ፡ +1-301-852-9972 (ሞባይል) ወይም በኢሜይል dufkac@hrw.org (ምዕራብ አፍሪካን በሚመለከት)

ለንደን፣ ካሪና ተርሳኪያን (እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ) ፡ +44-7903-503297 (ሞባይል) ፤ ወይም በኢሜይል tertsac@hrw.org (ሩዋንዳ እና ብሩንዲን በሚመለከት)

ለንደን፣ አንከ ቫን ዉደንበርግ (እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ) ፡ +44-207-713-2786፤ +44-77-11-66-4960 (ሞባይል) ፤ ወይም በኢሜይል woudena@hrw.org (ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎን በሚመለከት)

ለንደን፣ ቤን ራውለንስ (እንግሊዝኛ፣ ኪስዋሂሊ) ፡ +44-7-98-481-6013 (ሞባይል) (የአፍሪካ ቀንድን በሚመለከት)

ኒው ዮርክ፣ ጂሃን ሄንሪ (እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ) ፡ +1-212-216-1291፣ ወይም +1-917-443-2724 (ሞባይል)፣ ወይም በኢሜይል henryj@hrw.org (ሱዳንን በሚመለከት)